እንዲማሩ ። በሎዶቅያ ፡ ነገረ ፡ ምጽአት ፡ አለ ፡ ሠሪዐ ፡ ቤት ፡ የለም ፡ እነዚህ ፡ ያነን ፡ ተመልክተው ፡ ነገረ ፡ ምጽአትን ፡ እንዲያውቁ ፡ ነው ።

፲፯ ፡ ወበልዎ ፡ ለአክርጳ ፡ ኡቅአ ፡ መልእክተከ ፡ ዘተሠየምከ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ትፈጽም ።

አክርጳንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተሾምህበትን ፡ ሐዋርያነት ፡ እንድትፈጽም ፡ ዕወቅ፡ በሉት ።
እማኀኩክሙ ፡ ጽሒፍየ ፡ በእዴየ ፡ አነ ፡ ጳውሎስ ።

እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ በጄ ፡ ጽፌ ፡ እጅ ፡ ነሣኋችሁ ፡ (ሐተታ) በምን ፡ ይጽፈው ፡ ኑሯል ፡ ቢሉ ፡ ጽንዐ ፡ ፍቅሩን ፡ ስማጠየቅ ፡ ኃግሬዋለሁ ፡ ብላልኝ ፡ ፈትየዋለሁ ፡ ልበስልኝ ፡ ጠምቄዋለሁ ፡ ጠጣልኝ ፡ እንደማለት ፡ ነው ተዘከሩ ፡ መዋቅሕትየ ።

በክርስቶስ ፡ የሚኾን ፡ እስራቴንም ፡ አስቡ ።

ጸጋ ፡ ምስሌክሙ ። (፩ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፳፩ ፡ ፪ ፡ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡)

ጸጋ ፡ ይደረግላችሁ ፡ ይደርባችሁ ።

አሜን ፡　　　　በእውነት ፡

ተፈጸመ ፡ መልእክት ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ቈላስይስ ፡ ወተጽሕፈ ፡ በሮሜ ፡ ወተፈነወ ፡ በእደ ፡ ቲኪቆስ ።

በሮም ፡ የተጻፈ ፡ ለቈላስይስ ፡ ሰዎች ፡ በጢኪቆስ ፡ እጅ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከ ፡ ከታብ ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ።
ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።

እስጀምር ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

www.ethiopianorthodox.org